# በሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ የአፈጻጸም መመሪያ




ህዳር 2001 ዓ.ም
ሀዋሣ

## ማውጫ

## ክፍል አንድ

1.1 መግቢያ ------------------------------------------------------------------------------------1

1.2 አላማ-------------------------------------------------------------------------------------------2

1.3 የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች የሕዝብ ንቅናቄ መርሆዎች---------------------------------------3

1.4 የማስፈጸሚያ ስልቶች --------------------------------------------------------------------4

1.6 የሚጠበቁ ውጤቶች-----------------------------------------------------------------------5

## ክፍል ሁለት

2. የአስተባባሪ አካላት ሀላፊነትና ተግባር -------------------------------------------------7

2.1 በክልል ደረጃ ------------------------------------------------------------------------7

2.2 በዞን ደረጃ --------------------------------------------------------------------------8

2.3 በልዩ ወረዳ፣በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ----------------------------------8

2.4 በቀበሌ ደረጃ -----------------------------------------------------------------------9

## ክፍል ሦስት

3. የማኀበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነዱን ተፈጻሚ ለማድረግ የስነ -ሕዝብ ጉዳይ ፈጻሚ መ/ቤቶች ሚናና የአፈጻጸም ማኑዋል ትግበራ ----------------------12

3.1 የሥነሕዝብ ጉዳይ የፈጻሚ መ/ቤቶች ሚና- --------------------------------------12

3.2 የማኀበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ ትግበራ-------------------------------------15

## ክፍል አራት

4. የመወያያ ነጥቦች- -...........................................................................18

5. አባሪዎች -----------------------------------------------------------------------------23

# 1. መግቢያ

መንግሥት የህዝቡን ኑሮ ደረጃ በደረጃ ለማሻሻል የሚያስችሉ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማውጣት ሲተገብር ቆይቷል፤ አሁንም እየተገበረ ይገኛል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ሙሉ በሙሉ ማኀበራዊና ኢኮኖሚዊ ችግሮች ተቀርፈዋል ማለት አይቻልም። ልክ እንደሌሎቹ የሀገራችን ክልሎች ሁሉ የደቡብ ክልል ከፍተኛ የማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ያሉበት መሆኑን በተለያዩ ጊዜያት የሚወጡ መረጃዎች ያሳያሉ። እነዚህን ችግሮች በቋሚነት ለመቅረፍ ከሚያስችሉና መንግሥት ዘላቂና ፈጣን ልማትን እውን ለማድረግ ይፋ ካደረጋቸው ፖሊሲዎች አንዱ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ ነው። ይህ ፖሊሲ በዋነኛነት አላማ ያደረገው በሀገሪቱም ሆነ በክልሉ እየታየ ያለውን ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ከልማት ዕድገትና ከተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን በማድረግ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ነው።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት እ.ኤ.አ በ1994 ዓ.ም 10.4 ሚሊዮን የነበረው የክልሉ የህዝብ ቁጥር በ2007 በተደረገው ብሔራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሠረት 15.04 ሚሊዮን ደርሷል። ይህ አሀዝ በየአመቱ በአማካይ በ2.9% በማደግ ከ25 ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ 30 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይጠበቃል። ከላይ እንደተገለፀው የክልሉ መንግሥት የመሠረተ ልማት ለማስፋፋት የተለያዩ ስትራቴጂዎችንና ኘሮግራሞችን በመተግበር በከፍተኛ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም በፈጣን ሁኔታ የሚያድገውን ህዝብ መድረስ ግን አደጋች ሆኗል። በመሆኑም የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን በልማት እቅዶች ውስጥ አካቶ ተግባራዊ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው አቢይ አጀንዳ ሆኗል።

ይህንን ለማስኬድና በአስተማማኝና ዘላቂነት ባለው መልኩ ማስቀጠል ይቻል ዘንድ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲውን ማዕከል ባደረገ መልኩ ያልተማከለ አደረጃጀት የፈጠረውን አጋጣሚ በመጠቀም የሥነ-ሕዝብ ጉዳይን በሁሉም የልማት ሴክተሮች እቅድ ውስጥ ተካተው እንዲሠሩ በማድረግ በርካታ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል።

ከቤተሰብ ጋር የተገናዘበ የውልደት መጠን እንዲኖር ለማድረግ፣ኀብረተሰቡ በትምህርት ጥራት፣ሽፋንና ብቃት ላይ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ ፣የተፈጥሮ አካባቢ መራቆትና በረሃማነትን ለመከላከል፣የአካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ሕፃናትን ማኀበራዊ ደኅንነት ለማሻሻል፣ የሴቶችን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተሣትፎ ለማጠናከር፣የወጣቶችን የተዋልዶ ጤና ለማሻሻል፣ያልተፈለገ እርግዝናና የአባለዘር በሽታን ለመቆጣጠር ፣የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመግታት እንዲሁም በክልሉ ተንሠራፍተው የሚገኙትን ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

ለማስወገድ የሚያስችል ኅብረተሰቡን ማዕከልና ባለቤት ያደረገ የተቀናጀ ሕዝባዊ ንቅናቄ ማካሄድ ጠቀሜታው የጐላ በመሆኑ በስነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮች የማህበረሰብ ንቅናቄ ሰነድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደትም የማህበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሠነዱን በማዘጋጀት ከክልል እስከ ቀበሌ ባለው የአስተዳደር እርከን ውስጥ ኅብረተሰቡንና ተቋማትን በማቀናጀት ተግባራዊ ለማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

ለዚህ ንቅናቄ ተግባራዊነትም የተግባር እቅድና ጠንካራ ክትትልና ግምገማ ማድረግ ወሳኝ ግብአቶች ናቸው፡፡ ይህን ለማድረግ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ የመንግሥት አመራር አካላት፣ሴ/መ/ቤቶች፣ ህብረተሰቡ ፣መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣የሲቪክ ማህበራት፣ ት/ቤቶች የሃይማኖት ተቋማትና የሀገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ ሚና መጫወት ይገባቸዋል፡፡

በመሆኑም ይህ የአፈጻጸም መመሪያ የክልሉን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የማኅበረሰብ ግንዛቤ መፍጠርና የተግባራዊ እንቅስቃሴ መነሻ ሀይል በመሆን ንቅናቄውን ለማካሄድ የተዘጋጀ ሲሆን በውስጡም ዝርዝር የአፈጻጸም ስልቶችን፣የአስተባባሪ አካላት ሀላፊነትን፣የአስፈጻሚ መ/ቤቶች ሚናና ሌሎችን አባሪዎችንም አጠቃሎ ይዟል፡፡

## 2. ዓላማ

- የአፈጻጸም መመሪያው የህዝብ ንቅናቄውን በየደረጃው ያሉ አካላት እነማን ምን መፈጸም እንዳለበባቸው ለማሰየት፣ በውይይቱ የሚነሱ ዋና ዋና ጉዳዮችን ርዕሰ ጉዳዮችና የሚጠበቁ አብይ ውጤቶች ምን እንደሆኑ፣ የማህበረሰብ ንቅናቄው በምን አይነት ሁኔታ መካሄድ እንዳለበት በክልሉ ባሉ በተለያዩ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች፣ አንድ አይነት ወጥ አሰራር እንዲኖር ለማድረግ አስተባባሪ አካላቱ እንደማንዋል እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ነው፡፡
- የስነ-ህዝብና ልማት የስነ-ህዝብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ የአፈጻጸም ማኑዋል /መመሪያ ዋና ዓላማ ህብረተሰቡ በስነ-ህዝብና ልማት ጉዳዮች፣ በስርዓተ-ፆታና በተዋልዶ ጤና

ዙሪያ ባሉ ችግሮችና ሊወሰዱ በሚገቡ መፍትሔዎች ላይ የሰፊ ግንዛቤ ለመፍጠር የባህሪ ለውጥ ማምጣት ሆኖ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- በሁሉም የክለሉ ቀበሌዎች እየተከናወኑ ያሉ የልማት ስራዎች ከህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር እንዲጣጣም የሚያስችል አመለካከት መፍጠር፣
- የልማት ዕድገትን በአሉታዊ መልኩ እየተእየተፈታተኑ ያሉ ኃላቀርና ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ የህዝቡን የግንዛቤ ደረጃ ማሣደግ፣
- በተቀናጀ ቀጣይነት ባለው መልኩ የክልሉ ህብረተሰብ ለውጥ በማምጣት ህብረተሰቡ ተገቢውን የመፍትሔ እምጃ እንዲወስድ ማስቻል፡፡

## 3. የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች የሕዝብ ንቅናቄ መርሆዎች

በሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የሕዝብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ የኅብረተሰቡን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመቅረፍ የሚካሄደውን ጥረት ለማጠናከር ወሳኝ ሚና የሚጫወት ከመሆኑ አንፃር መተግበሩ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ለንቅናቄው ስኬታማነት የሚከተሉትን መርሆዎች አንግቦ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡

### 3.1 ሕዝቡን ማዕከልና ባለቤት ማድረግ፣

በፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ምክንያት ለሚከሰቱ የአገልግሎቶች አቅርቦት እጥረትና ሌሎች ማኀበራዊ ችግሮች ቀጥታ ተጠቂው ህዝቡ ከመሆኑ አንፃር መፍትሄ በማምጣት ረገድ ሕዝቡ ወሳኝ ሚና መጫወት ይገባዋል፡፡

በሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማህበረሰብ ንቅናቄ በዋናነት ባህላዊና ማኀበራዊ እሴቶችን እንዲሁም የተለያዩ አደረጃጀቶችን መሠረት ያደረገ መሆኑ የኅብረተሰቡን ተሣትፎ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ኅብረተሰቡ የራሱን ችግር በራሱ ተወያይቶ የመፍትሄ አቅጣጫ አስቀምጦና ለተግባራዊነቱም በጋራ ተንቀሳቅሶ የሚያመጣው ለውጥ በመሆኑ ኅብረተሰቡን ማዕከል ማድረጉን ያስገነዝባል፡፡

የዚህ ማቀጣጠያ ሰነድ ዋና አላማ ኅብረተሰቡ ከላይ በሚወርድለት መልኩ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ እድገቱን ጐታች የሆኑ ጉዳዮችን በራስ ተነሳሽነት አንጥሮ በማውጣት የመፍትሄው ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

### 3.2 የተቀናጀ አሠራር

በሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማህበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ ተግባራዊ ሊደረግና የተፈለገውን ግብ መምታት የሚችለው ከክልል እስከ ቀበሌ ባለው የሥልጣን እርከን ውስጥ ያሉ የሚመለከታቸው አካላትና መላ ኅብረተሰቡ በንቅናቄው ሂደት /ክትትልና ግምገማን ጨምሮ/ የነቃ ተሣትፎ ማድረግ ሲችሉና የተቀናጀ ሥራ ሲሰሩ ነው፡፡

### 3.3 ቁርጠኝነት

የማቀጣጠያ ሰነዱ ግቡን መምታት የሚችለው በአስፈጻሚ አካላቱም ሆነ በፈጻሚው ማኅበረሰብ ዘንድ የቁርጠኝነት መንፈስ ሲኖር ነው፡፡ ስለዚህ የሥነ-ሕዝብ እና ልማት ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ቀጣይነት ያለው ቁርጠኝነት በሁሉም በኩል ሊኖር ይገባል፡፡

### 3.4 የተጠናከረ የትብብር መንፈስ

የማቀጣጠያ ሰነዱ ማኅበረሰቡን ማዕከልና ባለቤት ያደረገ ሆኖ በየደረጃው የሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶች ፣መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣የሲቪክ ማህበራት፣የትምህርት ማዕከላት ፣የሃይማኖት ተቋማት፣ የግል ባለሀብቶች፣መገናኛ ብዙሃንና የሌሎችንም የልማት አጋሮች የተጠናከረ ተሣትፎ፣ አጋርነትና ትብብር የሚጠይቅ ነው፡፡

### 3.5 ተጠያቂነትና ሀላፊነት

ማቀጣጠያ ሰነዱ ተግባራዊ ሆኖ ግቡን የሚመታዊ በየደረጃው ያሉ አመራር አካላት የተሰጣቸውን ተግባራት በእቅድ ተመርተው ሥራውን በተጠያቂነትና በኃላፊነት መንፈስ ማከናወን ሲችሉ ነው፡፡ ለዚህም በየደረጃው ያሉ የሥነ-ሕዝብ ም/ቤቶችና የንቅናቄው አስተባባሪ አካላት በወጣው እቅድ መሠረት አፈጻጸሙን መከታተልና መገምገም እንዲሁም ማስተባበር ይኖርባቸዋል፡፡

## 4. *<u>የሚጠበቁ ውጤቶች</u>*

- ከቤተሰብና ኀብረተሰብ አቅም ጋር የተገናዘበ የውልደት መጠን እንዲኖር በክልሉ የግንዛቤ ደረጃ ያደገና ተገቢውን አዎንታዊ ባህሪይ ያመጣ ህብረተሰብ መኖር፣
- በየትምህርት ደረጃ ከጊዜ ወደ ጊዜ የጨመረ የሚገኘው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወደ መማሪያ ዕድሜ ክልል የመጣ ያለው ሕዝብ በትምህርት ሽፋን፣ ጥራትና ብቃት ላይ ያሳደረ ያለውን ጫና ተረድቶ የጋራ አመለካከት የያዘና የመፍትሄ ባለቤትለመሆን የተዘጋጀ ኀብረተሰብ ፣
- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ያመጣ የሚገኘውን የተፈጥሮ አካባቢ መራቆትና በረሃማነት ምርትንና ምር ማነትን ከማሽቆልቆል ባሻገር በቀጣይነት የሰው ልጅ የመኖር ዋስትና ፈ ኝ ያደረገው ንደሚገኝ ተረድቶ አፋጣኝ የመፍትሄ ባለቤት ለመሆን የወሰነ ኀብረተሰብ ፣
- የክልሉ ሕዝብ ጤናማና አምራች ንዲሆን ብቃትና ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ንዲያገኝ ከማስቻል ጐን ለጐን ከጤና ልማት ጋር ያልተጣጣመው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ያስከተለ ያለውን አሉ ዊ ጫና በመቅረፍ ረገድ ገንቢ ሚና ለመፍጠር የተዘጋጀ ሕዝብ፣
- የአካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንንና ሕፃናትን ማኀበራዊ ደህንነት ለማሻሻልና ሁለገብ ልማትን ለማከናወን የሚያስችል በመላ ኀብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠረ የአስተሳሰብ ለውጥ፣
- ሴቶችን ከማኀበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሣትፎዎች የሚገድቡ አስተሳሰቦችንና ተግባራትን ለማስወገድ የተጀመረ ሁለገብ ትግል ፣
- መብቶቻቸውን በሚያስከብሩ አዋጆችና ሕጐች ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው መብቶቻቸውን ለመጠቀም የተዘጋጁ ሴቶች መኖር፣
- ከፆ ዊ አድሎአዊ አመለካከት ተላቀው ሴት ከወንድ አቻዋ ኩል የመማር ድል ንዳለት በመገንዘብ ሴት ልጆችን ወደ ት/ቤት ለመላክ የወሰኑ ወላጆች
- በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን በማስቆም ረገድ ወንዶች ወሳኝ ሚና መጫወት እንደሚገባቸው የተረዳ ህብረተሰብ መኖር፣
- ከነበሩበት ኋላቀር አመለካከት ተላቀው ጤናቸውን ለመጠበቅ ቅደው ስከ ቀበሌ ባሉ መዋቅሮች በተቋቋሙ ጤና ድርጅቶች ተገቢውን የቅድመ ወሊድ፣ የወሊድና ድኅረ ወሊድ ክትትል ለማድረግ የወሰኑ እናቶች መኖር፣
- የተዋልዶ-ጤና መብቶችን ተገንዝበውና ተረድተው አገልግሎቱን በተገቢ ሁኔ በመጠቀም ካልተፈለገ ርግዝና፣አባለዘር በሽ ና ተያይዞ በሚከሰቱ የጤና ችግሮች ንዳይጋለጡ አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የተዘጋጁ ወጣቶች መኖር፣

- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያስከተለ ያለውን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ንዲሁም የጤና ችግር ለማስወገድ መተሳለፊያና መከላከያ መንገዶችን ተረድቶ ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግ የወሰነ ማህበረሰብ፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ለተጠቁ ወገኖች ቀጣይነት ባለው መልኩ አስፈላጊውን እንክብካቤ ለማድረግ የተዘጋጀ ህብረተሰብ መኖር፣
- በክልሉ በሰፊው ተንሰራፍተው በሚገኙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ የጋራ ግንዛቤና አወንታዊ ለውጥ ለማምጣት የወሰነ ህብረተሰብ መኖር፣

## *5. የማስፈጸሚያ ስልቶች*

- ከክልል ስከ ቀበሌ ደረጃ ያሉትን አስፈጻሚ አካላት የአመራር ሚናን በመጠቀም የማኀበረሰብ ውይይቶችን በማዘጋጀት ኀብረተሰቡ በሠነዱ ላይ ንዲወያይና የጋራ የመፍትሄ አቅጣጫ ንዲቀይስ ማስቻል፣
- በክልሉ በተዋረድ በሚገኙ የሥነ-ሕዝብ ም/ቤትና የሥነ-ሕዝብ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አማካኝነት ወደ ህዝብ እንደወርድ ማድረግ፣
- የተለያዩ የመንግሥ ዊና ሲቪክ አደረጃጀቶችን በማህበረሰብ ውይይቱ አካቶ እንዳአቅማቸውና እንደአስፈላጊነቱ ማሣተፍ፣
- በየቀበሌ ያሉ የሃይማኖት መሪዎችን፣ ዋቂ ግለሰቦችንና በጎ ፈቃደኞችን በመጠቀም ኀብረተሰቡን ማወያየት ፣
- በትምህርት ቤቶች የተቋቋሙ የሥነ-ሕዝብ ክበባትን በመጠቀም ሰነዱን ተፈጻሚ ማድረግ ፣
- በክልሉ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን በመጠቀም በሠነዱ ዓብይ ጉዳዮች ዙሪያ የሕዝቡንና የአመራሩን ግንዛቤ ማዳበር፣
- የትምህርት የጤናና የግብርና ሴክተር መ/ቤቶች በቀበሌ ደረጃ ያላቸውን የጤና ኤክስቴንሽንና የግብርና ልማት ባለሙያዎችን ርዕስ መምህራንና መምህራንን መጠቀም ሰነዱን ተፈጻሚ ማድረግ ፣

## *ክፍል ሁለት*

## *የአስተባባሪ አካላት ሀላፊነትና ተግባር*

በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኀበረሰብ ንቅናቄ በየደረጃው በበላይነት የሚመሩት በየእርከኑ የሚገኙ የስነ-ሕዝብ ም/ቤቶች ሲሆኑ የስነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደቶች ንቅናቄው ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ እንዲደረግ የቅርብ ክትትልና ዕገዛ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መሠረት የስነ-ሕዝብና ልማት የማኀበረሰብ ንቅናቄ ፈጻሚ አካላትና የሚያከናውኑት ተግባራት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.1 በክልል ደረጃ

### 2.1.1 የክልል ማኀበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ አካል

በክልል ደረጃ የሚካሄደው በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኀበረሰብ ንቅናቄ የሚመራው በክልሉ የስነ-ሕዝብ ም/ቤት ሆኖ የዕለት ተዕለት ሥራው በፋ/ኢ/ል/ቢሮ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት አስተባባሪነት ይሆናል፡፡

### 2.1.2 በክልል ደረጃ የአስተባባሪ አካል ተግባርና ሀላፊነት

የክልሉ በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኀበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ አካል የማኀበረሰብ ንቅናቄውን በክልሉ ውስጥ ለማካሄድ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፣

- በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኀበረሰብ ንቅናቄ የአሰልጣኞች ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፡፡
- በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኀበረሰብ ንቅናቄ ቅስቀሳና ትምህርት መገናኛ ብዙሃን በመጠቀም በስፋትና በቀጣይነት እንዲሰራጩ ያስተባብራል፣ይደግፋል፣የትምህርትና ቅስቀሳ ግብዓቶችን ያደራጃል፣ለሃዋሣ ከተማ አስተዳደር ለዞኖችና ለልዩ ወረዳዎች በወቅቱ ያሰራጫል፣አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡
- የተለያዩ ዘዴዎችን ወይም ሚድያዎችን በመጠቀም ስለማህበረሰብ ውይይቱ ትምህርትና ቅስቀሣ ያካሂዳል፣
- የትብብር መድረኮችን በክልል ደረጃ ያደራጃል፣በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የትብብር መድረኮች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡
- ለንቅናቄው ውጤታማነት የክልሉን ህዝብ ሀብትና አቅም መሠረት ያደረገ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን ይቀይሣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

- ለንቅናቄው ስኬታማነት ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣ የአፈጻጸም ግምገማ ያደርጋል፣ሪፖርትም በማጠናከር ለክልሉ ሥነ-ህዝብ ም/ቤት መደበኛ ስብሰባ ወቅት ያቀርባል፡፡

## 2.2 በዞን /በሃዋሣ ከተማ አስተዳደር ደረጃ

### 2.2.1 የዞን /የሃዋሣ ከተማ አስተዳደር የማኀበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ አካል

በዞን/በሃዋሣ ከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚካሄደው በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኀበረሰብ ንቅናቄ የሚመራው በዞኑ /በሃዋሣ ከተማ አስተዳደር የስነ-ሕዝብ ም/ቤት ሆኖ የዕለት ተዕለት ሥራው በዞኑ/ከተማ አስተዳደሩ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ይሆናል፡፡

### 2.2.2 <u>በዞን /በሃዋሣ ከተማ አስተዳደር ደረጃ የአስተባባሪ አካል ተግባርና ሃላፊነት</u>

- የዞኑ/የሃዋሣ ከተማ አስተዳደር የማኀበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ አካል ንቅናቄውን በዞኑ/ከተማ አስተዳደሩ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፣
- የተለያዩ ዘዴዎች ወይም ሚዲያዎችን በመጠቀም ስለ ማህበረሰብ ውይይቱ ትምህርት ቅስቀሣ ያካሂደል፣
- በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኀበረሰብ ንቅናቄ የአሰልጣኞች ስልጠናዎችን በዞን/በሃዋሣ ከተማ ደረጃ ያዘጋጃል፣ይሰጣል፣ተፈጻሚነቱንም ፣ይከታተላል፤
- የትብብር መድረክ በዞን/በከተማ አስተዳደር ያደራጃል፣በልዩ ወረዳና በክልል ደረጃ ከሚገኙ የትብብር መድረኮች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤
- ለንቅናቄው ውጤታማነት የዞኑን/ የሀዋሣ ከተማ አስተዳደሩን ህዝብ ሀብትና አቅም መሠረት ያደረገ ገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን ይቀሰቅሣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣ ያደርጋል፣ሪፖርቱን በማጠናቀር ለዞኑ/ከተማ ሥነ-ህዝብ ም/ቤት
- የትምህርት ቅስቀሣ ግብአቶችን ያደራጃል፣ ለክፍለ ከተማ አስተዳደርና ለወረዳዎች በወቅቱ ያሰራጫል አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
- ለንቅናቄው ስኬታማነት ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣ የንቅናቄውን የአፈጻጸም ግምገማ ያደርጋል፣ ሪዓርቱን በማጠናከር ለዞኑ ከተማ አስተዳደሩ ስነ-ህዝብ ም/ቤት መደበኛ ስብሰባ ወቅት ያቀርባል፣ ለክልሉ ስነ-ህዝብ ም/ቤትና ለፋይ/ኢ/ል/ቢሮም ሪፖርቱን ይካል፣

## 2.3 በልዩ ወረዳ፣በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ

### 2.3.1 የልዩ ወረዳ /ወረዳ/ ከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተማ የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ አካል

በልዩ ወረዳ / ወረዳ / ከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚካሄደው በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኅበረሰብ ንቅናቄ የሚመራው በልዩ ወረዳው /በወረዳው/በከተማ አስተዳደሩ የስነ-ሕዝብ ም/ቤት ሆኖ የዕለት ተዕለት ሥራው በልዩ ወረዳው/ ወረዳው/ ከተማ አስተዳደር/ ክፍለ ከተማው/ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ይሆናል፡፡

### 2.3.2 <u>በልዩ ወረዳ /በወረዳ/ በከተማ አስተዳደር /በሀዋሣ ክፍለ ከተማ ደረጃ የማህበረሰብ ንቅናቄ የአስተባባሪ  አካላት ተግባርና ሀላፊነት</u>

የልዩ ወረዳው /የወረዳው/ የከተማ አስተዳደር የሀዋሣ ክፍለ ከተማ  የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ አካላት ንቅናቄውን በልዩ ወረዳው /በወረዳው በከተማ አስተዳደር በሀዋሣ ክፍለ ከተማ ውስጥ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት በሀላፊነት ያከናውናል፣

የተለያዩ ዘዴዎች ወይም ሚድያ ዎችን በመጠቀም ስለማህበረሰብ ውይይት ትምህርትና ቅስቀሣ ያካሂዳል፡፡

- በልዩ ወረዳው /በወረዳው /ከተማ አስተዳደር /በሀዋሣ ክፍለ ከተማ በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ አወያዮችና የማኅበረሰብ ውይይት አመቻቾች ሥልጠና ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፣ ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፣
- የትብብር መድረክ በልዩ ወረዳ /በወረዳ/ በከተማ አስተዳደር በሀዋሣ ክፍለ ከተማ ደረጃ ያደራጃል፣ በዞን ደረጃ ከሚገኙ የትብብር መድረኮች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣
- ለንቅናቄው ስኬታማነት ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣ሳምንታዊ የአፈጻጸም ግምገማ ያደርጋል፣ሪፖርትም በማጠናከር ለልዩ ወረዳው /ወረዳው/ ከተማ አስተዳደር ለሀዋሣ ክፍለ ከተማ ሥነ-ህዝብ ም/ቤት የመደበኛ ስብሰባ ወቅት ያቀርባል፣ ከዚህ በተጨማሪ ልዩ ወረዳው ለክልሉ ሥነ-ሕዝብ ም/ቤትና ለፋ/ኢ/ል/ቢሮ፣ ወረዳውና የከተማ/ ክፍለ ከተማ/ አስተዳዳሩ ለዞኑ ስነ-ሕዝብ

ም/ቤትና ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት መምሪያ የተጠናቀረውን የአፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት ይልካሉ፤

## 2.4 በቀበሌ ደረጃ

2.4.1 የቀበሌ የማኅበረሰብ ንቅናቄ  አስተባባሪ አካል

በቀበሌ ደረጃ በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኅበረሰብ ንቅናቄ በበላይነት የሚመራው ይህንን ተግባር ለማስፈጸም በቀበሌ ውስጥ በሚቋቋመው የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ አጋር መ/ቤቶችና አካላት በአባልነት የሚገኙበት የቀበሌ የሥነ-ሕዝብና ልማት የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

2.4.2 *__በቀበሌ ደረጃ የማኅበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴው አወቃቀር__*

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የቀበሌው ሥራ አስኪያጅ | - ሰብሳቢ |
| 2. | የቀበሌው የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተወካይ | ፀሐፊ |
| 3. | ‹‹ የግብርና ልማት ሠራተኞች ተወካይ | አባል |
| 4. | ‹‹ የመንግሥት ት/ቤት ርዕሰ መምህር(ተወካይ) | አባል |
| 5. | ‹‹ የበጎ ፍቃድ መልእክተኞች ተወካይ | አባል |
| 6. | በቀበሌው ታዋቂ ግለሰብ ወይም የአገር ሽማግሌ | አባል |
| 7. | ‹‹ የሴቶች ፌዴሬሽን ሊ/መንበር | አባል |
| 8. | ‹‹ የወጣቶች ፌዴሬሽን ሊ/መንበር | አባል |
| 9. | ‹‹ የመረዳጃ ዕድር ሰብሳቢ | አባል |

ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች አካላትም የኮሚቴው አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

2.4.3 የአስተባባሪ ኮሚቴው ተግባርና ሀላፊነት

- በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኅበረሰብ ንቅናቄ በቀበሌው ውስጥ በበላይነት ይመራል፣ያስተባብራል፣
- የቀበሌውን የማኅበረሰብ ንቅናቄ ዝርዝር ዕቅድ ያወጣል፣ተግባራዊ እንዲሆን ያስተባብራል፣ይደግፋል፣

- የተለያዩ ዘዴዎች ወይም ሚዲያዎችን በመጠቀም ስለ ማህበረሰብ ውይይቱ ትምህርትና ቅስቀሣ ያካሂደል፣
- በቀበሌው በጎጥ /በንዑስ ቀበሌ/ ደረጃ የማኅበረሰብ ንቅናቄ የማቀጣጠያ ውይይቶችንና መደበኛ የውይይቱ መድረኮችን ያዘጋጃል፣ይመራል፣
- በጎጥ ደረጃ በሚካሄዱት የማኅበረሰብ ንቅናቄ የማቀጣጠያ ውይይቶች የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣የግብርና ልማት ሠራተኞች፣መምህራን እና ሌሎችንም ብቁ የሆኑና ቋንቋውን በሚገባ የሚሰሙና የሚናገሩ ነዋሪዎች በአመቻችነት ይመድባል፣ አፈጻጸሙንም ይደግፋል፣ ይከታተላል፣
- በቀበሌው በሚገኙ ት/ቤቶች በጎጥ በንዑስ ቀበሌ ደረጃ በሚዋቀሩ ቡድኖች የማኅበረሰብ ንቅናቄ የማቀጣጠያ ውይይቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
- የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚያቀርቧቸውን የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ማህበረሰቡ በስፋት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይቀሰቅሳል፣ያበረታታል፣አገልግሎቶቹም ተሟልተው መቅረባቸውን ይከታተላል፣ካልቀረቡ በወቅቱ ለበላይ አካል ሪፖርት ያደርጋል፣ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል።
- የሴት ልጅ ትምህርት ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣የጎዳና ተዳዳሪዎች ፣ደጋፊ የሌላቸው አረጋውያን፣አካል ጉዳተኞች ፣ወዘተ... ማህበረሰቡ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲያደርግ ያስተባብራል፣ከሌሎች አካላት የሚገኘውንም ግብዓት በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል፣
- የስነ-ሕዝብና ልማት ነክ መረጃዎች በቀበሌ ውስጥ እንዲደራጁ ያደርጋል፣ማኅበረሰቡም መረጃውን ተጠቃሚ እንዲሆን ያበረታታል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
- በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኅበረሰብ ውይይት ማቀጣጠያ የትብብር መድረኮችን በቀበሌ ደረጃ ያደረጃል፣በወረዳ ደረጃ ከሚገኝ ተመሣሣይ የትብብር መድረክ ጋርም ግንኙነት ያደርጋል፣
- ለማኅበረሰብ ንቅናቄ ስኬታማነት ድጋፋዊ ክትትልና፣ የአፈጻጸም ግምገማ ያደርጋል፣ወርሃዊ የአፈጻጸም ሪፖርትም በማጠናቀር በቀበሌው አስተባባሪ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ላይ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ለወረዳው የስነ-ሕዝብ ም/ቤትና የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ይልካል፣

## *ክፍል ሦስት*

## የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነዱን ተፈጻሚ ለማድረግ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ፈጻሚ መ/ቤቶች ሚናና የአፈጻጸም ማኑዋል ትግበራ

### 3.1 የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ፈጻሚ መ/ቤቶች ሚና

### 3.1.1 የጤና ሴክተር ሚና

የጤና ሴክተር ከክልል እስከ ወረዳ በተቋቋሙት በሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቶች ውስጥ አንዱ አባል መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሥነ-ሕዝብና ልማት የማኅበረሰብ ንቅናቄን የማስተባበርና የመተግበር ሥራ እንደሴክተሩ ተግባር አድርጎ ይወጣል፡፡

በክልል፣ በዞን፣በልዩ ወረዳ፣ በወረዳና በከተማና ክፍለ ከተማው አስተዳደር ደረጃ የሚገኙ በጤና ሴክተር መዋቅር ውስጥ የሚገኙ የአመራር አካላት በየእርከኑ በሚደረጉ በማቀጣጠል እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፍ ድርሻቸውን የሚወጡ ከመሆኑም በላይ በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ ጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሥነሕዝብ ጉዳይ ላይ በየቀበሌውና በየጎጡ የሚካሄዱትን የማኅበረሰብ ውይይቶችን ከሚመለከታቸው ጋር ሆነው በግንባር ቀደምትነት እንዲያመቻቹና እንዲያስተባብሩ አመራር ይሰጣሉ፡፡ የቀበሌው የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተወካይ የቀበሌው የሥነሕዝብና ልማት የማኅበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴ ፀሐፊ ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን የተቀሩትም በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሁሉ ኮሚቴው በሚሰጣቸው በማስተባበርና በማመቻቸት ሥራ በንቃት ይሳተፋሉ፣

### 3.1.2 የትምህርት ሴክተር ሚና

የትምህርት ሴክተር ከክልል እስከ ወረዳ በተቋቋሙት በሥነሕዝብ ምክር ቤቶች ውስጥ አባል መ/ቤት እንደሆኑ መጠን ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሥነ-ሕዝብና ልማት የማኅበረሰብ ንቅናቄን የማስተባበርና የመተግበር ሥራን እንደሴክተሩ ተግባር አድርጎ ይወጣል።
በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚገኙ በትምህርት ሴክተር ውስጥ ያሉ አመራር አካላት በየእርከኑ በሚደረጉ በማቀጣጠያ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በትኩረት በመሳተፍ የድርሻቸውን የሚወጡ ከመሆኑም በላይ በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የሴክተሩ ባለሙያዎች (ርዕሰ-መምህራንና መምህራን) በሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ላይ በየቀበሌውና በየጎጡ የሚካሄዱትን የማኅበረሰብ ውይይቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆነው በግንባር ቀደምትነት እንዲያመቻቹና እንዲያስተባብሩ አመራር ይሰጣሉ።
በቀበሌው ያለ የመንግሥት ት/ቤት ርዕሰ መምህር ወይም ተወካይ የቀበሌው የሥነ-ሕዝብና ልማት የማኅበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ሌሎች መምህራንና ርዕሰ መምህራንም ኮሚቴው በሚሰጣቸው የማስተባበርና የማመቻቸት ሥራ ይሣተፋሉ።

### 3.1.3 <u>የግብርና ልማት ሴክተር ሚና</u>

የግብርና ልማት ሴክተር ከክልል እስከ ወረዳ በተቋቋሙት በሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቶች ውስጥ አባል መ/ቤት እንደመሆኑ መጠን ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሥነ-ሕዝብና ልማት የማኅበረሰብ ንቅናቄን ማስተባበርንና መተግበርን እንደሴክተሩ ተግባር አድርጎ ይወጣል።
በክልል፣በዞን፣በልዩ ወረዳ፣ በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚገኙ በግብርና ልማት ሴክተር ውስጥ የሚገኙ አመራር አካላት በየእርከኑ በሚደረጉ የማቀጣጠል እንቅስቃሴዎች በትኩረት በመሳተፍ የድርሻቸውን የሚወጡ ከመሆኑም በላይ በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ የሴክተሩ ባለሙያዎች (የግብርና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች) በሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ላይ በየቀበሌውና በየጐጡ የሚካሄዱትን የማኅበረሰብ ውይይቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆነው በግንባር ቀደምትነት እንዲያመቻቹና እንዲያስተባብሩ አመራር ይሰጣሉ።

በቀበሌው የሚገኙ የግብርና ልማት ሠራተኞች ተወካይ የቀበሌው የሥነ-ሕዝብና ልማት የማኅበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን ሌሎች የግብርና

ልማት ሠራተኞችም ኮሚቴው በሚሰጣቸው የማስተባበርና የማመቻቸት ሥራ ውስጥ ይሳተፋሉ፣

### 3.1.4. <u>በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሴክተር የሥነሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ሚና</u>

#### 3.1.4.1 የማስተባበርና ሙያዊ /የቴክኒክ ድጋፍ በተመለከተ

የክልሉ የስነ-ህዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የስራ ሂደት በክልል ደረጃ የሚገኙ የስነ-ህዝብ ጉዳይ ፈጻሚ የሆኑ ሴ/ር መ/ቤቶችና መያዶችን የማንቀሳቀስና የማስተባበር ሥራ የሚወጣ ሲሆን በልዩ ወረዳና በዞን ደረጃ ለሚካሄደው ንቅናቄ ቴክኒካዊ እገዛ ያደርጋል፡፡ በዞኖች ደረጃ የሚገኙ የስነ- ህዝብ ጉዳይ ፈጻሚ ሴ/ር መ/ቤቶችና የሀዋሣ ከተማና የዞኖች የስነ-ህዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር የሥራ ሂደት በሀዋሣ ከተማና በዞኖች ሥነሕዝብ ነክ ሥራ የሚሠሩ መያዶችን የማንቀሳቀስና የማስተባበር ሥራን የሚያከናውን ሆኖ ከሥሩ ላሉ ወረዳዎችና ሀዋሣ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ክፍለ ከተሞች ለሚካሄደው ንቅናቄ ሙያዊ እገዛና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደርና በሀዋሣ ክፍለ ከተሞች ደረጃ የሚገኙ የሥነ-ህዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር የሥራ ሂደት በልዩ ወረዳ፣በወረዳና በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚገኙ የስነ-ህዝብ ጉዳይ ፈጻሚ ሴ/ር መ/ቤቶችና ሥነሕዝብ ነክ ሥራ የሚሠሩ መያዶችን የማንቀሳቀስና የማስተባበር ሥራ የሚወጣ ሆኖ ከሥሩ ላሉ ለከተማና ገጠር ቀበሌያት አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም እገዛና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

የሕዝብ ንቅናቄውን ለማቀጣጠል እንዲረዳ በተዘጋጀው ሰነድ ላይ የክልሉ የስነ-ህዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የስራ ሂደት ለዞኖች ፣ለሀዋሣ ከተማ አስተዳደርና ለልዩ ወረዳዎች እንዲሁም በክልሉ ለሚገኙ የስነ-ህዝብ ጉዳይ ፈጻሚ ለሆኑ ሴክተር መ/ቤቶች የአሠልጣኞች ስልጠና ይሰጣል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ሀዋሣ ከተማን ጨምሮ ዞኖች ከሥሮቻቸው ላሉ ወረዳዎች ወይም ክፍለ ከተማዎች የአሠልጣኞች ስልጠና ይሰጣሉ፣ እንዲሁም በተዋረድ ወረዳዎችና ልዩ ወረዳዎች፣ የሀዋሣ ከተማ ክፍለ ከተሞችንና ከተማ አስተዳደሮች ከበታቻቸው ላሉ ቀበሌያት ውስጥ ለሚገኙት ለቀበሌ የማኀበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትና አመቻቾች ሥልጠና ይሰጣሉ፡፡

### 3.1.4.2 የማቴሪያል እና የገንዘብ ድጋፍ

**የማቴሪያል ድጋፍ**

የሕዝብ ንቅናቄውን በተሳካ ሁኔታ ለማስኬድ እንዲቻል ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በየደረጃው ባሉ በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሴክተር መ/ቤቶች አማካኝነት በወቅቱ ሊዘጋጁና ሊቀርቡ ይገባል፡፡ ከነዚህ ማቴሪያሎች ውስጥ የማህበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድና የአፈጻጸም መመሪያው በዋናነት ይገኙበታል፡፡ ሁለቱም ሰነዱ ለእያንዳንዱ የማኅበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴ አባላትና አመቻቾች ተሚልቶ መዳረሱ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶች ማለትም ማስታወሻ ደብተር፣እስኪቢሪቶ፣ ወዘተ፣ በየደረጃው ለሚገኙ አመቻቾችና ለማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ሊሚሉ የሚገባ ሲሆን ለወረዳ አስተባባሪዎች ለክትትል ሥራ የሚያግዝ ተሽከርካሪ ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡

**የገንዘብ ድጋፍ**

- በየእርከኑ ያሉ የስነ-ሕዝብ ም/ቤቶች ለንቅናቄው ሥራ የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ ከመንግሥት በጀትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ያፈላልጋሉ፡፡

የገንዘብ ምንጭ ከየት መገኘት እንዳለበት የዞንና ልዩ ወረዳ የስነ-ህዝብ ም/ቤት ከክልሉ ስነ-ህዝብ ም/ቤት ጋር ውይይት አድጕ ውሣኔ እነደሚተላለፍ ይጠበቃል፣

## 3.2 <u>የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ ትግበራ</u>

የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ ሰነድ በዋናነት የሚተገበረው የሥነ-ህዝብ ክበባት በተቋቋመባቸው ት/ቤቶች፣ በየቀበሌውና በየጎጡ ደረጃ ነዋሪውን ህዝብ ሰብስቦ በማወያየትና ወደ ውሣኔ ደረጃ እንዲደርሱ በማድረግ ነው፡፡

ይሁንና ከላይ የተጠቀሰውን ሃሣብ ለማሳካት በየደረጃው ያሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አጋር መ/ቶችና ድርጅቶች በሥራው ላይ በትኩረት ሊሳተፉበትና የየራሳቸውን ድርሻ ሊወጡ ስለሚገባ በተቋማት ደረጃም የማስተባበርና የማንቀሳቀስ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡

### 3.2.1 <u>በቀበሌና በጎጥ ደረጃ የሚካሄድ የሥነ-ሕዝብ የማኅበረሰብ ውይይት</u>

- ❖ አንድ የማኅበረሰብ ውይይት ከ70 እስከ 100 ሰው የሚይዝ ሲሆን በአንድ አካባቢ (ጎጥ) የሚኖሩ ሰዎች ( ወንዶችና ሴቶች) በአንድ ቡድን ውስጥ ቢካተቱ ይመረጣል፡፡ በአንድ ቀበሌ ውስጥ እንደየሰው ብዛት ብዙ የማኅበረሰብ ውይይት ቡድን ሊኖር ይችላል፡፡
- ❖ የማህበረሰብ ውይይቱ በክልሉ በሚገኙ በሁሉም ቀበሌያት ይደረጋል፡፡
- ❖ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ በቀበሌው የሚገኙ የመንግሥት ት/ቤት ርዕሰ-መምህራን፣ የግብርና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ወይም 10ኛ ክፍልና በላይ የተማሩ ፈቃደኛ የሆኑ የቀበሌው ኗሪዎች የሥነ-ህዝብ ማህበረሰብ ውይይት አመቻቾች (facilitators) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- ❖ በቀበሌው ሥራ አስኪያጅ ሰብሳቢነት የሚመራው የቀበሌው የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ ኮሚቴ በቀበሌው ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የሥነ-ሕዝብ ማኅበረሰብ ውይይት ቡድኖችን አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ይገመግማል፣ የአፈጻጸም ችግር ባለበት ሁሉ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡
- ❖ የሥነ-ህዝብና ልማት ማህበረሰብ ውይይት አወያይና አመቻቾች የአካባቢውን ቋንቋ ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆን አለባቸው፡፡
- ❖ የሥነ-ሕዝብና ልማት ማኅበረሰብ ውይይት ቡድን አባላት ውይይት አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ የሚገባው ሲሆን የመሰብሰቢያው ቦታ፣ ቀንና ሰዓት በአባላቱ የሚመረጥና አብዛኛው ሰው የተስማማበት ሊሆን ይገባል፡፡
- ❖ አወያዮች የማኅበረሰብ ውይይት በተደረገ ቁጥር ለዚሁ በተዘጋጀው ቅጽ (የውይይቱን ርዕስ፣ የተሣታፊውን ሕዝብ ብዛት፣የመሰብሰቢያ ቦታና ሰዓት፣ የተወሰነውን ውሣኔ ወይም አብዛኛው ሰው እንደመፍትሄ የሰጣቸው ሃሣቦች) አካትተው ለቀበሌው የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ፀሐፊ በየጊዜው ሊያቀርቡ ይገባል፡፡
- ❖ በሰነዱ ላይ በሚገኙ ሁሉም የውይይት ርዕሶች ላይ ሕዝቡ በሚገባ ተወያይቶ እስከሚጠናቀቁ ድረስ የሥነ-ሕዝብ የማኅበረሰብ ውይይት ቡድኖች ውይይታቸውን ሣያቋርጡ ይቀጥላሉ፡፡
- ❖ የቀበሌው የስነ-ህዝብ ንቅናቄ አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲቆሙ እስካልወሰኑ ድረስ ማንኛውም የስነ-ህዝብ ማህበረሰብ ውይይት ቡድን በተለመደው ሁኔታ መሰብሰብንና መወያየቱን ፈጽሞ ማቋረጥ የለበትም፡፡

### 3.2.2 <u>በትምህርት ቤቶች የሚካሄድ የሥነ-ሕዝብ ማኅበረሰብ ውይይት</u>

- በትምህረት ቤቶች የሚካሄደው የስነ-ህዝብ የማህበረሰብ ውይይት የስነ-ህዝብ ክበባት በተቋቋመባቸው ት/ቤቶች ብቻ ነው፡፡
- የትምህርት ቤት የሥነ-ሕዝብ ማኅበረሰብ ውይይት የሚመራው በሥነ-ሕዝብ ማኅበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴ ሲሆን የኮሚቴው አስተባባሪ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ምክትል ርዕሰ መምህር ሆኖ ፀሐፊው ደግሞ የሥነ-ሕዝብ ክበብ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ የኮሚቴው አባላት ደግሞ የሥነሕዝብ ክበብ አመራር አካላት ይሆናሉ፡፡
- በማኅበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴ አማካኝነት የትምህርት ቤቱን ተማሪዎች፣ መምህራንና ሠራተኞችን ሁሉ ያሰባሰበ አጠቃላይ ስብስባ ተደርጎና ስለጉዳዩ ገለፃ ተደርጎላቸው ውይይቱን መቼ መጀመር እንዳለባቸው በጋራ ሊወሰኑ ይገባል፡፡በዚያ ውሣኔ መሠረት በሰነዱ ላይ የተቀመጡ ሁሉም መወያያ ርዕሶች ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውይይት ተደርጉባቸውና የመፍትሄ ሀሣብ ተሰጥቶባቸው ውይይቱ ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡
- ውይይቱን የሚመራው የአስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም በርሱ የተወከለው ሰው ይሆናል፡፡
- በእያንዳንዱ የውይይት ጊዜ ቃለ ጉባዔ በሚገባ ተይዞ የተደረሰበትን ውሣኔ በሚያሳይ ሁኔታ ለዚህ በተዘጋጀው ቅጽ ለወረዳው ሥነ-ሕዝብ ምክር ቤት ፀሐፊ ለሆነው የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በየጊዜው ሪፖርት ማድረግ ይገባል፡፡

# <u>ክፍል አራት፡</u> የመወያያ ነጥቦች

## 4.1 <u>ከትምህርት አንፃር</u>

1. በአካባቢያችሁ ድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት በሙሉ ወደ ት/ቤት ገብተዋል? ካልገቡ ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል? ለወደፊቱስ መፍትሄው ምን መሆን አለበት?
2. በቀበሌያችሁ የሚገኙት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለተማሪዎች መማሪያ የሚሆኑ የመማሪያ መፃህፍቶችና ሌሎች የትምህርት ቁሣቁሶች በሚገባ ተሟልተዋል?
3. ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ሣይጨናነቁ ማለትም በአንደኛ ደረጃ በአንድ ክፍል 50 ተማሪዎች ለመማር ችለዋል? ካልቻሉስ ምክንያቱ ምንድነው? ምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?
4. በአካባቢያችሁ በየአንዳንዱ ቤት ውስጥ የሚገኙ ህፃናት በአግባቡ የተመገቡ፣ የለበሱና ንፅህናቸው ተጠብቆ ትምህር ቸውን የተማሩ ነው? ካልሆነስ የችግሩ ምንጭ ምንድነው ብላችሁ ትገም ላችሁ? መፍትሄውስ ምንድነው?
5. በአካባቢያችሁ ባሉት ትምህርት ቤቶች በአመቱ ከሚመዘገቡት ተማሪዎች የሚያቋርጡ አሉ? የሚያቋርጡ ከሆነስ ምክንያቱ ምንድነው?
6. ወላጆች ብዙ ልጆችን በመውለዳቸው ምክንያት ለማስተማር ባለመቻላቸው የሚያቋርጡ ልጆች የሉም? ካሉስ በቀጣይ ኅብረተሰቡ ችግሩን ለመፍ ት ምን ሊያደርግ ይገባል? ከመንግሥትስ ምን ይጠበቃል ?

## 4.2 ከግብርናና ገጠር ልማትና አካባቢ ጥበቃ አንፃር

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ዛፎች ለምን ለምን አገልግሎት ትጠቀሙባቸዋላችሁ? በሚቆረጡት ዛፎች ምትክ ችግኝ የመትከል ሁኔታ ምን ይመስላል? ዛፎችን ሣይተኩ ለረጅም ጊዜ እየቆረጡ መጠቀም፣ በህብረተሰቡ ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድነው? ይህንን ችግር ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት?
2. በአካባቢያችሁ በደን ውድመትና የአፈር መሸርሸር ምክንያት የተከሠተ ያለ ችግር አለ? ካለ ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል? በቀጣይ የወደሙ ደኖችን መልሶ በመትከልና ያሉትን በመንከባከብ ከኅብረተሰቡም ሆነ ከመንግሥት ምን ይጠበቃል?
3. በዚህ አካባቢ በእያንዳንዱ አርሶ አደር እጅ የሚገኘው የእርሻ መሬት በቂ ነው? ካልሆነ ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል?
4. የመሬት ፍላጎትና የመሬት ይዞ በአባወራ ደረጃ ያመጣ ያለው ችግር አለ? ካለ በቀጣይ ምን ሊደረግ ይገባል?

5. በዚህ አካባቢ ማረስ እየቻሉ የእርሻ መሬት የሌላቸው ሰዎች አሉን? ካሉ ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል? መፍትሔውስ?
6. በቤተሰብ ደረጃ የነፍስ ወከፍ የምግብ ህል ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ ንዲባባስ ያደረገው ምክንያት ምንድነው?
7. ከጊዜ ወደ ጊዜ የጨመረ የሚገኘው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በምግብ ህል ፍላጎት ላይ ጫና አላሳደረም? ካሳደረ ያሳደራቸው ጫናዎች ምንድናቸው? ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ከህብረተሰቡና ከመንግስት ምን ይጠበቃል?

## *4.3 ከጤና ሴክተር አንፃር*

1. በአካባቢያችሁ ያሉት የጤና ተቋማት ከህዝቡ የሕክምና ፍላጐት አንፃር በቂ ናቸው? ካልሆኑ ምክንያቶቹ ምን ይመስላችኋል? መፍትሄውስ ምን መሆን አለበት?
2. በጤና ተቋማቶች ውስጥ በቂ የህክምና ባለሙያዎች /ዶክተሮችና ነርሶች/ አሉ? ያሉት የህክምና ባለሙያዎች ለአካባቢው ህ/ሰብ ተገቢውን ህክምና እየሰጡ ናቸው? ካልሆነ መፍትሄው ምን ይመስላችኋል?
3. በጤና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ የህክምና መሣሪያዎችና መድሀኒቶች ከህብረተሰቡ ፍላጐት ጋር የተጣጣሙ ናቸው? ካልሆነ ምን መደረግ አለበት?
4. ተዋልዶ ጤና ማለት ምን ማለት ነው ይመስላችኋል? የተዋልዶ ጤና ችግሮች የሚባሉትስ? ስለ ተዋልዶ ጤና መረጃ የምታገኙት ከየት ነው?
5. በአካባቢያችሁ የተዋልዶ ጤና አገልግሎት የሚሰጡ በቂ ተቋማት አሉ? ካሉ ወጣቱ አገልግሎቱን በሚፈለገው መጠን እያገኛችሁ ነው? ካልሆነ ምክንያቶቹ ምንድናቸው? ለወደፊቱስ ምን መደረግ አለበት?
6. በዚህ አካባቢ ጥንቃቄ የጐደለው /ህገ-ወጥ/ ውርጃ ይፈፀማል ? ከተፈጸመ ከዚህ ጋር በተያያዘ የደረሱ ጉዳቶች ምን ምን ናቸው?
7. በአካባቢያችሁ የሚገኙት የጤና ጣቢያዎች ጥንቃቄ የተሞላው የውርጃ አገልግሎት ይሰጣሉ? በህጋዊ መንገድ በጤና ተቋማት ውስጥ ጥንቃቄ የተሞላው ውርጃ እንደሚካሄድ ምን ያህል ታውቃላችሁ?
8. በአካባቢያችሁ ሴቶች በእርግዝና ወቅት ጤና ተቋማት በመሄድ የህክምና ክትትል ያደርጋሉ? የማያደርጉ ከሆነ ምክንያቶቹ ምን ምን ናቸው? ይህንን ባለማድረጋቸው ምን ምን ችግሮች ይከሰታሉ? በቀጣይ ይህንን ችግር ለማስወገድ ከህብረተሰቡ ምን ይጠበቃል?

9. በዚህ አካባቢ አብዛኛዎቹ ሴቶች የሚወልዱት የት ነው? በጤና ተቋማት፣ በቤት ውስጥ ወይስ በሌላ ቦታ? ለምን?
10. በዚህ አካባቢ ከወሊድ በኃላ እናትየውና ህፃኑ በጤና ተቋማት በመሄድ የህክምና ክትትል የማድረግ ልምድ አለ? ከሌለ ወደፊት ምን መደረግ አለበት?

## 4.4 *<u>ከማህበራዊ ጉዳይ አንፃር</u>*

- በአካባቢያችሁ ሥራ አጥ የሆኑ ሰዎች የሉም? ካሉ ለምን ሥራ አጥ የሆኑ ይመስላችኋል?
- በዚህ አካባቢ የሥራ ባህልና ክቡርነት ምን ይመስላል?
- ሥራ አጥነትን በዘላቂነት ለመፍታት ከህብረተሰቡና ከመንግስት ምን ይጠበቃል?
- በአካባቢያችሁ የጐዳና ተዳዳሪ ልጆች አሉ? ከእናንተ አካባቢስ ወደጐዳና የወጡ ልጆች አሉ? ካሉ መንስኤው ምን ይመስላችኋል? ይህንን ችግር ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት?
- ከዚህ አካባቢ ተሰደው ወደ ሌላ አካባቢ የሄዱ ሰዎች አሉ? ካሉ ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል?
- ሰዎች ከዚህ አካባቢ ተሰደው በመሄዳቸው ምክንያት በዚህ አካባቢ ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም ጥቅም አለ?
- ከሌላ አካባቢ ወደዚህ ተሰደው የመጡ ሰዎች አሉ? በዚህ ምክንያት በዚህ አካባቢ ላይ የደረሰ ጉዳት ወይም ጥቅም አለ?
- በአጠቃላይ ከስደት ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ ችግሮችን ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት?

## 4.5 *<u>ከሴቶችና ህፃናት ጉዳይ አንፃር</u>*

- በዚህ አካባቢ ወንዶች በአብዛኛው የሚሰሯቸው ሥራዎች ምን ምን ናቸው?ሴቶች የሚሰሯቸው ስራዎችስ? ይህ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
- ወንዶች የሚሰሯቸውን ስራዎች ሴቶች ቢሰሩት ሴቶች የሚሰሯቸውን ሥራዎች ደግሞ ወንዶች ቢሰሩት ምን ችግር ይኖሯል?
- በዚህ አካባቢ ከሴትና ከወንድ የሚከበረው ማነው? ለምን
- በአካባቢያችሁ ከሚማሩት ተማሪዎች አብዛኛዎቹ ሴቶች ናቸው ወይስ ወንዶች? ይህ የሆነው ለምን ይመስላችኋል? ከልጆቻችሁ መካከል ት/ቤት ሄደው እንዲማሩ የምትፈቅዱት ለወንዶች ነው? ወይስ ለሴቶች?ሴት ልጆችን ማስተማር ጥቅሙ ምንድነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
- ብዙ ጊዜ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡት ወንዶች ናቸው ወይስ ሴቶች? ለምን? ለወደፊቱ ይህንን ችግር ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት?

- በዚህ አካባቢ ሴቶች ከወንዶች እኩል የንብረት ባለቤት ናቸው? ካልሆኑ ምክንያቶቹ ምንድናቸው? የንብረት ባለቤት የሆኑና ያልሆኑ ሴቶች ሲነፃፀሩ በውሣኔ ሰጪነታቸው ላይ ያለው ልዩነት ምንድነው?
- በቤተሰብ ውስጥ በሚከናወኑ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ማለትም ከብት ለመሸጥ፣ ንብረት ለመግዛትም ሆነ ለመሸጥ፣ ልጆችን ትምህርት ቤት እንዲሄዱ ለማድረግ ወ.ዘ.ተ የሚወስነው ማነው? ባል፣ ሚስት፣ወይስ ሁለቱም? ለምን? ለወደፊቱ እንዴት ቢደረግ የተሻለ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
- ሴቶች የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ ከህብረተሰቡ ምን ይጠበቃል?
- በአካባቢያችሁ የልማት ሥራዎች ላይ የሴቶችና የወንዶች የሥራ ድርሻ ምን ይመስላል? ይህ በመሆኑ በሴቶች ህይወት ላይ ያለው ተጽዕኖ ምንድነው? ወደፊትስ ምን መደረግ አለበት?
- በአካባቢያችሁ ምን ያህል ሴቶች በኃላፊነት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ?
- ከወንዶች አንፃር በኃላፊነት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሴቶች ቁጥር በቂ ነው? ካልሆነ ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል? ይህንን ለማስተካከል ለወደፊቱ ምን መደረግ አለበት? የህብረተሰቡስ ሚና ምን መሆን አለበት?
- በዚህ አካባቢ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው? የሚያደርሱት ጉዳትስ ምንድነው?
- በነዚህ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በአብዛኛው የሚጠቁት እነማን ናቸው?
- ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ ከህብረተሰቡ ምን ይጠበቃል? እስካሁንስ ምን ጥረት እየተደረገ ይገኛል?

## *4.6 ከወጣቶች ጉዳይ አንፃር*

- ተዋልዶ ጤና ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል? የተዋልዶ ጤና ችግሮች የሚባሉትስ? ስለተዋልዶ ጤና መረጃ የምታገኙት ከየት ነው?
- በአካባቢያችሁ ወጣት ተኮር የተዋልዶ ጤና ማዕከላት አሉ? ካሉ ምን ምን ሥራዎችን ይሠራሉ?
- ያልተፈለገ እርግዝና መንስኤዎቹ ምን ምን ይመስላችኋል? እንዳይከሰት ማድረግ የሚገቡን ጥንቃቄዎች ምን ምን ናቸው? ከተከሰቱስ በኋላ ችግሮቹን እንዴት መከላከል እንችላለን?

- **ጥንቃቄ የጐደለው ውርጃ** (unsafe abortion ) **እና ጥንቃቄ የተሞላው ውርጃ** (safe abortion ) **ልዩነታቸው ምን ይመስላችኋል**?
- በአካባቢያችሁ ወጣት ተኮር የመዝናኛ ማዕከላት አሉ? ካሉ ከወጣቱ ፍላጐት አንፃር በቂ ናቸው? ካልሆነ ምክኒያቱ ምን ይመስላችኋል? ወደፊትስ ምን መደረግ አለበት?

## *4.7 ከኤች.አይቪ/ ኤድስ ስርጭት አንፃር*

- *ዋና ዋናዎቹ የኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ምንድናቸው? የጥንቃቄ መንገዶቹስ ምንድናቸው? ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣በማህበረሰብና በአገር ደረጃ የሚያደርሰው ተጽእኖ ምንድነው? ኤች.አይ.ቪ.ኤድስን ለመከላከል ከህብረተሰቡ ምን ይጠበቃል?*

# 4. አባሪዎች

**ሠንጠረዥ 1**: በሥነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኅበረሰብ ውይይት ዓቢይ የመወያያ ርዕሰ ጉዳዮች፣የትኩረት ነጥቦች፣ ከውይይቱ የሚጠበቁ ውጤቶችና የመረጃ ምንጮች

| ተቁ | ዓብይ የመወያያ ርዕሰ ጉዳይ | በውይይቱ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጭብጦች /በዋናነት ሊነሱ የሚገባቸው ጉዳዮች/ | ከውይይቱ የሚጠበቁ /የሚገኝ ውጤት | ምርምራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሥነ-ሕዝብና ልማት | | | |
| | 1.1 ሥነ-ሕዝብና ትምህርት | - ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በትምህርት ሽፋን፣ ብቃትና ጥራት ላይ እያሳደረ ያለውን ጫና ኅብረተሰቡ ግንዛቤ ኖሮት አዎንታዊ ለውጥ ማምጣቱ፣ ከቤተሰብ አቅም ጋር ያልተመጣጠነ የልጆች ቁጥር ቤተሰብ ልጆቹን በሚገባ እንዳያስተምር እንቅፋት እንደሚሆን በጥልቀት መረዳት | - ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ወደ መማሪያ ዕድሜ ክልል እየገባ ያለው የህፃናት ቁጥር በትምህርት ብቃትና ጥራት እንዲሁም ሽፋን ላይ እያሳደረ ያለውን ጫና ተረድቶ የጋራ አመለካከት የያዘና የመፍትሄ ባለቤት ለመሆን የተዘጋጀ ኅብረተሰብ መኖር<br>- ከኢኮኖሚ አቅም ጋር የተመጣጠነ ቤተሰብ መኖር ልጆች ተገቢውን ትምህርት ማግኘት የሚያስችላቸው መሆኑን የተረዳና አዎንታዊ ባሕርይ ለውጥ ለማምጣት የወሰነ ህ/ሰብ | |
| | 1.2 ሥነ-ሕዝብ ግብርና ፣የተፈጥሮ አካባቢና የምግብ ዋስትና | - ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት እያመጣ የሚገኘውን የተፈጥሮ አካባቢ መራቆትና በረሃማነት፣ ምርትና ምርታማነትን ከማሽቆልቆል ባሻገር በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ ስለሚያደርግ ኅብረተሰቡ ይህን በጽኑ ተረድቶ ተግባራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ማስቻል፣ | -ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የተፈጥሮ አካባቢ መራቆትና በረሃማነት፣ ምርትና ምርታማነትን ከማሽቆልቆል ባሻገር በቀጣይነት የሰው ልጅ የመኖር ዋስትናን ፈታኝ እያደረገው እንደሚገኝ ተረድቶ አፋጣኝ የመፍትሄ ባለቤት ለመሆን የተዘጋጀ ህ/ሰብ | |
| | 1.3 ሥነ-ሕዝብና ጤና | - ከጤናው አገልግሎት አቅርቦት ጋር የማይመጣጠን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ተገቢውን የጤና አገልግሎት ማግኘት ስለማይችልና መንግሥትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ለሚገኘው የሕዝብ ቁጥር ተገቢውን የጤና አገልግሎት ለማዳረስ አቅሙ ውስን መሆኑን በመረዳት ኅብረተሰቡ የተመጠነ የቤተሰብ መጠን እንዲኖረው<br>- የተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን በሚገባ መጠን አለመጠቀም ለስነ-ህዝብና ተያያዥ ችግሮች የሚያጋልጥ መሆኑን መረዳት | -ከጤና ልማት ጋር ያልተጣጠመ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት እያስከተለ ያለውን አሉታዊ ጫና በመቅረፍ ረገድ ገንቢ ሚና ለማበርከትና የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ለመጠቀም የተዘጋጀ ኅብረተሰብ መኖር ፣ | |
| | 1.4 ሥነ-ሕዝብና ማኀበራዊ ችግሮች | - በክልሉ በሰፊው ተንሠራፍተው የሚገኙ ማኀበራዊ ችግሮች ማለትም<br>- ያለዕድሜ ጋብቻ<br>- ሥራ አጥነት<br>- ጐዳና ተዳዳሪነት<br>- ሴተኛ አዳሪነት<br>- አካል ጉዳተኝነት፣ ወዘተ...<br>ወሳኝ የሥነ-ሕዝብና ልማት ችግሮች መሆናቸውን ህብረተሰቡ ተረድቶ ተግባራዊ እርምጃ እንዲወስድ ማስቻል | - የጐዳና ተዳዳሪዎችን፣ ሴተኛ አዳሪዎችን፣የአካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንንና ሕፃናትን ማኀበራዊ ደህንነት ለማሻሻልና ሁለገብ ልማትን ለማከናወን የሚያስችል በመላ ኅብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠረ ግንዛቤ መኖር፣ | |

...... የቀጠለ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 | ሥርዓተ ፆታና ልማት | | | |
| | 2.1 ሥርዓተ -ፆታና ትምህርት | -ህብረተሰቡ የሴቶችን የመማር ጠቀሜታ በሚገባ በመረዳት ሴት ልጆችን ወደ ት/ቤት ለመላክ እንዲወሰን ማብቃት፣<br>-ህብረተሰቡ ሴቶች ከወንዶች እኩል በኢኮኖሚ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዘርፎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንደሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ማስቻል፣ | - ከተዛባ ፆታዊ አመለካከት ተላቆ ሴት ከወንድ አቻዋ እኩል የመማርና በሁለገብ የልማት እንቅስቃሴዎች፣ መሣተፍ እንደምትችል በመገንዘብ ሴቶች ትምህርትን እንዲማሩ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የተዘጋጀ ህብረተሰብ | |
| | 2.2 ሥርዓተ-ፆታ- ተዋልዶ ጤና | - በሰፊው የተንሠራፉት የተዋልዶ ጤና ችግሮች ሴቶችን ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ስለሚዳርጉ ችግሩ ከሥር መሠረቱ ለማስወገድ የመላ ኅብረተሰቡ ዘርፈ-ብዙ ተሣትፎ ወሳኝ መሆኑን ማስገንዘብ፣ | - ሴቶችና መላ ኅብረተሰቡ የተዋልዶ ጤና መብቶችን ተገንዝበውና ተረድተው አገልግሎቱን በተገቢ ሁኔታ በመጠቀም ካልተፈለገ እርግዝና ፣አባለዘር በሽታና ተያይዞ በሚከሰት የጤና ችግሮች እንዳይጋለጡ በመላ ሕዝብ ዘንድ የተፈጠረ የጋራ አመለካከት | |
| | 2.3 ሥርዓተ- ፆታና -የንብረት ባለቤትነት | የማኀበረሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች የንብረት ባለቤትነትን መብት በማጐናፀፍ የልማቱ እኩል ተሣታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ መላ ሕዝቡ አዎንታዊ የባሕርይ ለውጥ በማምጣት የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማስቻል፣ | - በክልሉ በገጠርም ሆነ በከተማ የሴቶችን ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኑሮአቸውን ለማሻሻል ዘርፈ-ብዙ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ የቀረጠ ህብረተሰብ መኖር፣ | |

.......... የቀጠለ

| ተ ቁ | ዓብይ የመወያያ ርዕሰ ጉዳይ | በውይይቱ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጭብጦች /በዋናነት ሊነሱ የሚገባቸው ጉዳዮች/ | ከውይይቱ የሚጠበቁ /የሚገኝ ውጤት | ምርምራ |
|---|---|---|---|---|
| | 2.4 ሥርዓተ -ፆታና የሥራ ስምሪት | -ኅብረተሰቡ የተዛባ የሥርዓተ ፆታ አመለካከትን በማስወገድ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች እንደ ዕውቀታቸውና ችሎታቸው በተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኙላቸው የስራ መስኮች እንዲሠማሩ የግንዛቤና የአመለካከት ክፍተት መሙላት | -ኋላቀርና የተዛባ የስርዓተ-ፆታን በማስወገድ ሴቶች ከወንዶች እኩል ሥራ መሥራት እንደሚችሉና የተሻለ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ መሠማራት እንደሚችሉ የተገነዘበና ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ የወሰነ ህብረተሰብ | |
| | 2.5 ሥርዓተ ፆታና የፖለቲካ ተሣትፎ | -ሴቶች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት እኩል የሆነ የፖለቲካ ተሣትፎ እንዲያደርጉና የውሣኔ ሠጪነት ሚናቸውን እንዲያጐለብቱ መላው ህብረተሰብ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማስቻል፣ | -በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የሴቶች ፖለቲካዊ ተሣትፎና የውሣኔ ሠጪነት ሚና ለልማት ያለውን በጎ አስተዋጽኦ በመረዳት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ የተዘጋጀ ህብረተሰብ | |
| | 2.6 ሥርዓተ ፆታና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች | -በክልሉ በሰፊው ተንሠራፍተው የሚገኙት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በሴቶች ላይ የአካልና የአእምሮ ጠባሳ የሚፈጥሩና በልማት ተሣትፎአቸው ላይ እንቅፋት እንደሚሆኑ በመገንዘብ ኅብረተሰቡ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ጠንክሮ እንዲዋጋ ማስቻል፡ | ስለ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በቂ ግንዛቤ የወሰደና ድርጊቱን ለማስቆም የአመለካከትና የባሕርይ ለውጥ ለማምጣት የወሰነ ህብረተሰብ | |
| | 2.7 ሥርዓተ ፆታና ኤችአይቪ/ኤድስ | - ሴቶች በማኅብረሰቡ ዘንድ በተሰጣቸው ዝቅተኛ ሥፍራ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ የኢኮኖሚና የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ በመሆናቸውና የወሲብ ጥቃትን ተከትሎ በቫይረሱ የመያዝ ዕድላቸውን ከፍ ስለሚያደርግ ይህንን ተገንዝቦ ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ በቀጣይነት ለማድረግ በመላ ኅብረተሰቡ ዘንድ ቁርጠኝነት እንዲኖር ማስቻል፣ | - ሴቶች በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ከወንዶች ይልቅ ለቫይረሱ የተጋለጡ መሆናቸውን በዕኑ ተረድቶ ችግሩን ለማስወገድ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ የቆረጠ ህብረተሰብ መኖር፣ | |

| ተ ቁ | ዓብይ የመወያያ ርዕስ ጉዳይ | በውይይቱ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጭብጦች /በዋናነት ሊነሱ የሚገባቸው ጉዳዮች/ | ከውይይቱ የሚጠበቁ /የሚገኝ ውጤት | ምርምራ |
|---|---|---|---|---|
| 3. | ሥነ-ሕዝብና ተዋልዶ ጤና | | | |
| | 3.1 የእናቶችና ሕፃናት ተዋልዶ ጤና | - በክልላችን በሰፊው የሚስተዋለውን የእናቶችና ሕፃናት ስቃይና ሞት በመቀነስና በሕይወት የመኖር ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ አዎንታዊ አስተሳሰብና አመለካከት በመላ ኅብረተሰብ ዘንድ እንዲሠርጽ ማስቻል፣ | -ከተዋልዶ ጤና ጋር በተያያዘ የሚሞቱትን እናቶችንና ሕፃናትን ቁጥር ለመቀነስ አዎንታዊ የሆነ አስተሰሰብና አመለካከት ለማምጣት የተዘጋጀ ህ/ሰብ | |
| | 3.2 ስነ-ህዝብና የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት | - የኅብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ አቅም ያገናዘበ የልጆች ቁጥር እንዲኖር በመወሰን የተሻለና ዘመናዊ ኑሮ ለመኖር የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆን ምርታማና ጤናማ ቤተሰብን ለመፍጠር ኃላፊነት የሚሰማው ኅብረተሰብ እንዲኖር ማስቻል፣ | -የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ጠቀሜታን በመረዳት ተጠቃሚ ለመሆን የተዘጋጀ ህብረተሰብ መኖር | |
| | 3.3 የወጣቶች ተዋልዶ ጤና | -የተዋልዶ ጤና መብቶችን ተገንዝበውና ተረድተው አገልግሎቱን በተገቢው ሁኔታ በመጠቀም ካልተፈለገ እርግዝና ፣አባለዘር በሽታና ተያይዞ በሚከሰት የጤና ችግሮች ላለመጋለጥ በመላ ኅብረተሰቡ በተለይም በወጣቱ ዘንድ የጋራ አስተሳሰብና አመለካከት ማስፈን፣ | -የወጣቶች-ተዋልዶ ጤና ችግሮች እያስከተሉ የሚገኙትን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ሥነ-ልቦናዊ ቀውሶችን በደንብ ተረድቶ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት የቆረጠ ህብረተሰብ | |
| | 3.4 ስነ-ህዝብና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ | -ኤች.አይ.ቪ /ኤድስ/ እያስከተለ ያለውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የጤና ችግሮችን ለማስወገድ መተላለፊያና መከላከያ መንገዶችን ተረድቶ ተገቢውን ጥንቃቄ የሚያደርግ ኅብረተሰብ እንዲኖር ማስቻል፣ | -የችግሩን አሣሣቢነት ተረድቶ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት የወሰነ ህብረተሰብ | |

ሰንጠረዥ 3 በስነ-ሕዝብና ልማት ጉዳዮች የማኅበረሰብ ንቅናቄ ማቀጣጠያ የአፈጻጸም ሂደት ምልክታ

| የእርከን ደረጃ | ግብዓቶች | ትምህርትና ቅስቀሳ | ድጋፋዊ ክትትል | ሪፖርት |
|---|---|---|---|---|
| ክልል | - በፋ/ኢ/ል/ቢሮ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ለንቅናቄው ማስፈሚያ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ዞን፣ሃዋሣ ከተማ አስተዳደርና ልዩ ወረዳ መድረሳቸውን ያረጋግጣል፡፡<br>- ክፍተቶችን ለመሙላት የተለያዩ ድጋፎችን ይፈልጋል፣ሌሎች ሥራዎች እንደአስፈላጊነቱ ይፈጽማል፡፡ | - የተለያዩ ሚዲያዎችን በመ ጠቀም ንቅናቄውን ውጤታማ ሊያደርጉ  የሚችሉ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን ሠፊ የዜና ሽፋን በማሰጠትና ጋዜጣዊ መግለጫዎችን በመስጠት የማኅበረሰብ ንቅናቄውን የማቀጣጠል ሥራዎችን ይሰራል፣<br>-የትምህርትና ቅስቀሳ ህትመቶች ዞን፣ሃዋሣ ከተማ አስተዳደርና ልዩ ወረዳ መድረሳቸውን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፣ | - የሥራ ሂደቱ የሱፐር ቪዥን ቡድን በማቀቋም ዞኖችንና ልዩ ወረዳዎችን በመከፋፈል የንቅናቄውን አካሄድ ይከታተላል፣<br>- የተቀናጀ ድጋፋዊ ክትትል ለዞኖችና ለልዩ ወረዳዎች ይሰጣል፣<br>- የተቀናጀ የንቅናቄው ሱፐር ቪዥን ቼክ ሊስት ያዘጋጃል፡ | የንቅናቄውን ሂደትና የአፈጻጸም ሪፖርት ለሚመለከታቸው ሁሉ በወቅቱ ያስተላልፋል፣ |
| ዞን/ሀዋሣ ከተማ አስተዳደር | -በፋ/ኢ/ል/ መምሪያ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት ለንቅናቄው ሂደት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ወረዳ/ክፍለ ከተማ እንዲደርሱ ያደርጋል፣<br>- ለንቅናቄው የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ግብዓቶችን በመለየት በወቅቱ ያቀርባል፣ | - የማኅበረሰብ ሬዲዮኖችን፣ ባነሮችን፣ቢል ቦርዶችን ፣በራሪ ወረቀቶችን ፣ወዘተ... በመጠቀም ለንቅናቄው ጠቃሚነት ያላቸው የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎችን ያካሂዳል፣<br>- የትምህርትና ቅስቀሳ ህትመቶችን ለወረዳዎች/ክፍለ-ከተሞች ያሰራጫል፣ | - በዞኖች/ሃዋሣ ከተማ አስተዳደር ንቅናቄውን የዞኑ/የከተማው የስነሕዝብ ም/ቤት በበላይነት የሚመራው ሲሆን የስነሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት  በባለቤትነት ያስተባብራል፣<br>- የስራ ሂደቱ ወደ ወረዳዎች/ክፍለ ከተሞች በመውረድ በቢሮው በተዘጋጀው ቼክ ሊስት መሠረት ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣<br>- የስነ-ሕዝብ ባለሙያዎች ወረዳዎችን/ ክፍለ-ከተሞችን ተከፋፍለው ድጋፋዊ ክትትሉን እንዲያካሂዱ ያደርጋል፣ | - የንቅናቄው የአፈጻጸም ሪፖርት ከክልል በሚተላለፉ ፎርማቶች መሠረት በማጠናቀር ለክልሉ ፋ/ኢ/ል/ቢሮ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡ |

....... የቀጠለ

| የእርከን ደረጃ | ግብዓቶች | ትምህርትና ቅስቀሳ | ድጋፋዊ ክትትል | ሪፖርት |
|---|---|---|---|---|
| ልዩ ወረዳ /ወረዳ/ ከተማ አስተዳደር | የፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት የሥነሕዝብ ጉዳዮች ማስተ/መተግ/ ዋና የሥራ ሂደት ለንቅናቄው ሂደት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ለሁሉም ቀበሌዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፣<br>- ተጨማሪ ግብዓቶች በሚገኙበት ሁኔታ ላይ ውሣኔ ይሰጣል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፡፡<br>- የልዩ ወረዳው /ወረዳው/ ከተማ አስተዳደርና ካቢኔው ለንቅናቄው አስፈላጊ ድጋፍ እንዲሰጡ ያስተባብራል፣፣ | - የአካባቢውን ኅብረተሰብ ለመድረስ የሚያስችሉ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችን ማለትም በራሪ ወረቀቶችን፣ማይክሮፎኖች ን፣ወዘተ... በመጠቀም ትምህርታዊ ቅስቀሳዎችን ያካሂዳል፣ | - የማኅበረሰብ ንቅናቄውን የሥነ-ሕዝብ ም/ቤት በበላይነት የሚመራው ሲሆን የፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ማስተ/መተግ/ዋና የሥራ ሂደት ንቅናቄውን በባለቤትነት ያስተባብራል፣<br>- በእያንዳንዱ ቀበሌ ውስጥ የማኅበረሰብ ውይይት አስተባባሪ ኮሚቴ እንዲዋቀር ያደርጋል ፡፡<br>- በየሣምንቱ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ውስጥ በቀበሌና ደረጃ በመገኘት ድጋፋዊ ክትትል ያደርጋል፣<br>- በእያንዳንዱ ቀበሌ ከሚኖረው ውይይት ሊያደርግ ከሚችለው ህዝብ ውስጥ ቢያንስ 80% በንቅናቄው መሳተፈን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፡፡<br>- በእያንዳንዱ ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን ሕዝብ በማሰባሰብ ለውይይት የሚመቸውን ቀንና ቦታ እንዲመርጥ ያደርጋል፡<br>-ከላይ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት መደበኛ ያልሆነ የማኅበረሰብ ንቅናቄ ውይይት በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የቅርብ ክትትል ያደርጋል፣<br>- መደበኛ ያልሆነ የማኅበረሰብ ንቅናቄ ውይይት እንደተጠናቀቀ መደበኛ የማኅበረሰብ ውይይት በእያንዳንዱ ቀበሌ ውይይት ማድረግ ከሚችለው ቢያንስ 80% የኅብረተሰብ ክፍል የተሳተፈበት እንዲካሄድ የቅርብ ክትትል ያደርጋል፡፡ | - የንቅናቄው ሂደትና አፈጻጸም ሪፖርት ለወረዳና ከተማ አስተዳደር ከዞን፣ ከልዩ ወረዳና ከክልል በሚተላለፉ የተቀናጁ ፎርማቶች መሠረት ከቀበሌዎች ከሚሰበሰቡ መረጃዎች ጋር ተዳምሮ ለዞን/ ለክልል የሥነሕዝብ ጉዳዮች ማስተ/መተግበር ዋና የሥራ ሂደት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ |

... የቀጠለ

| የእርከን ደረጃ | ግብዓቶች | ትምህርት ቅስቀሳ | ድጋፋዊ ክትትል | ሪፖርት |
|---|---|---|---|---|
| ቀበሌ | የቀበሌ የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ አካል ለንቅናቄው ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በቀበሌው ውስጥ ተሟልተው መገኘታቸውን ይከታተላል፣ያረጋግጣል። | - የአካባቢውን ኀብረተሰብ ለመድረስ የሚችሉ የመገናኛ ዘዴዎችን ማለትም የኀጥ መሪዎችን ወይም ጥሩንባ በመጠቀም ነዋሪዎቹን በማሰባሰብ መልእክቶችን ያስተላልፋል፣ | - በቀበሌ ደረጃ የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ ኮሚቴ ንቅናቄውን በበላይነት ይመራል፣<br>- ለንቅናቄው ስኬታማነት አስተባባሪ ኮሚቴው በቀበሌው የሚገኙ መምህ ራን፣የልማት ጣቢያ ሠራተኞችን፣ በጎ ፍቃደኞችን ፣የሴቶችንና የወጣቶች ማኅበራት አባላቶችንና ሌሎችን ለንቅናቄው ይጠቅማሉ የሚሏቸውን ክፍሎችንና ግለሰቦችን በስፋት ማንቀሳቀስ ይጠበቅበታል፣<br>- የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ ኮሚቴው የሚታዩ ክፍተቶችን ከልዩ ወረዳው፣ ከከተማው ወይም ወረዳው ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤትና ከስነ-ሕዝብ ም/ቤት ጋር እየተመካከረ እንዲሟሉ ያደርጋል። | - የቀበሌው የማኅበረሰብ ንቅናቄ አስተባባሪ ኮሚቴ በንቅናቄው ወቅት የተከናወኑ ተግባራትን ለልዩ ወረዳው/ ከተማው፣ ወይም ወረዳው ፋ/ኢ/ል/ጽ/ቤት የሥነሕዝብ ጉዳዮች ማስተባበርና መተግበር ዋና የሥራ ሂደት በሪፖርት ማጠናቀሪያ ፎርማቶች መሠረት ሪፖርት ያደርጋል። |